# የውጭ በታን ዳግም ማጠንጠን (ሪኢማጂኒንግ አውትዶር ስፔስ)፡

## ምግብ ቤቶችና የችርቻሮ ሱቆች

*ለተስፋፉና ለአዳዲስ የውጭ (አውትዶር) መቀመጫ የወጡ መመሪያዎች (ጋይድላይንስ)*




coronavirus.dc.gov

DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

እንደ የዲስትሪክት ደረጃ-አንድ ዳግም መክፈት (ፌዝ ዋን ሪኦፐኒንግ) አካል የውጭ ቦታ በሚከተሉት መንገዶች ትራንስፎርም ሊደረግ (ሊለወጥ) ይችላል፡

- **ምግብ ቤቶች** የእግረኛ መንገድ (ሳይድዎክ) ቦታ፣ ጠባብ መተላለፊያ መንገዶች (አሊስ)፣ የመኪና ማቆሚያ መስመሮችና የጉዞ መስመሮች ወደ **መናፈሻዎች (ፓርክለትስ) እና የውጭ መመገቢያ መቀመጫ** ሊቀይሩ ይችላሉ።
- **የማህበረሰብ ድርጅቶች** (በተለይ ደግሞ የአከባቢ አማካሪ ኮሚሽኖች [ኤ.ኤን.ሲ.ዎች፣ ዋና ጎዳና (መይን ስትሪት) ድርጅቶች፣ ወይም የቢዝነስ መሻሻል ዲስትሪክቶች [ቢ.አይ.ዲ.ዎች]) ሙሉውን የመኪና ማቆሚያ ብሎክ ወይም የጉዞ መስመር(ሮች) ወደ **ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች ፣** ጠባብ መተላለፊያ መንገድ (አሊ) ወይም ሌላ የህዝብ ቦታ (ፓብሊክ ስፔስ) ክፍሎች ደግሞ ወደ የመመገቢያ ፕላዛዎች መቀየር ይችላሉ።
- **ቸርቻሪዎች** የውጭ ቦታን ለ **የመንገድ ጠርዝ ማንሳትና ማድረስ (ከርብሳይድ ፒክአፕ ኤንድ ደሊቨሪ)** ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ምግብ ቤቶች ዳግም የመክፈትና የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ስርጭት የመቀነስ ዋነኛ ሚዛን መጠበቅን ለማሳካት፣ ይሄን ስራ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እንዴት መካሄድ እንዳለበት የሚረዳ ዲስትሪክቱ መመሪያዎች (ጋይድላይንስ) አውጥቷል። እነዚህ መመሪያዎች ከዲ.ሲ. ሄልዝ (ጤና)፣ ከጤና መቆጣጠርና መከላከል ማእከል (ሲ.ዲ.ሲ.) እና ከብሔራዊ/አለም አቀፋዊ ምርጥ ልምዶች ከተገኙ መመሪያዎች የተውጣጡ ናቸው።

## ተግባራዊነት

ብቁ ለሆኑ ምግብ ቤቶችና ለሌላ የምግብ ነክ ድርጅቶች በህንጻው የመስራት ፈቃዳቸው (ሰርቲፊኬት ኦፍ ኦኩፓንሲ) በሚፈቅደው መሰረት አዲስ የውጭ መቀመጫ ማስፋትና መፍጠር ለጊዜው ይፈቀድላቸዋል።

ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች፣ ፕላዛ፣ ወይም የጠባብ መተላለፊያ መንገድ (አሊ) መዘጋቶች ሊጠየቁ የሚችሉት በቢዝነስ መሻሻል ዲስትሪክቶች (ቢ.አይ.ዲ.)፣ በዋና ጎዳና (መይን ስትሪት) ድርጅቶች፣ ወይም በአከባቢ አማካሪ ኮሚሽኖች (ኤ.ኤን.ሲ.) ብቻ ነው።

## የህዝብ ቦታ አጠቃቀም

እነዚህ መመሪያዎች የህዝብ ቦታ እንዴት ለሰፋና አዲስ መቀመጫ መጠቀም እንደሚቻል ያሳያሉ። ይህ አንድ መጠን ለሁሉም ይገጥማል አይነት አቀራረብ አይደለም፣ እና የንግድ ቦታዎች የብቻ፣ የንግድ ዲስትሪክቶችና አከባቢዎች (ነይበርሁድስ) ፍላጎቶች ለሟሟላት የሚረዱ መስተካከል የሚችሉ አማራጭ ዝርዝሮች ያቀርባል። አመልካቾች ለአዳዲስና ለማስፋፊያ መቀመጫ በሚከተሉት ቦታዎች ማመልከት ይችላሉ፡

### ምግብ ቤቶች ብቻ

*የእግረኛ መንገዶች (ሳይድዎክስ)*

- ወዲያውኑ በምግብ ቤቱ ፊት ለፊት፣ እና
- ከጎን ባለ ቦታ፣ ይህ የሚሆነው ከጎን ካለው የመሬት ወለል ንግድ ወይም ንብረት ባለቤት የጽሁፍ ፈቃድ ከተሰጠ ነው።

*የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች*

- *ወዲያውኑ በምግብ ቤቱ ፊት ለፊት (ፓርክለት ተብሎ የሚጠራው)፣ እና*
- *ከጎን ባለ ቦታ፣ ይህ የሚሆነው ከጎን ካለው የመሬት ወለል ንግድ ወይም ንብረት ባለቤት የጽሁፍ ፈቃድ ከተሰጠ ነው።*

### የማህበረሰብ ድርጅቶች ብቻ

ስትሬቸሪ የሚባል መሸጫ: ሙሉውን የመኪና ማቆሚያ ብሎክ ወይም የጉዞ መስመር(ሮች)፣ እና

የመመገቢያ ፕላዛ: የጠባብ መተላለፊያ መንገድ (አሊ) ወይም ሌላ የህዝብ ቦታ (ፓብሊክ ስፔስ) ክፍሎች።

## የህዝብ ቦታ ንድፍ መስፈርቶች

ንግድ ቦታዎች በጎን ያለውን የእግረኛ መንገድ ስፋት በትክክል ለመወሰን በመንገድ ጠርዝና በህንጻው ግድግዳ ያለውን ስፋት መለካት ይኖርባቸዋል። የሚከተሉት ለሁሉም የህዝብ ቦታዎች ጥቅሞች የሚያስፈልጉ አነስተኛ ርዝመቶች መስፈርቶች ናቸው፣ አንዳንዶቹ በወለሉ በቴፕ ግልጽ የሆነ ምልክት ያስፈልጋቸዋል፡

- በእግረኛ መንገድ ቢያንስ የ6-ጫማ ግልጽ እግረኞች የሚሄዱበት መተላለፊያ (አንዳንድ ቦታዎች ያለውን የእግረኛ መንገድ ጽዳት (ክሊራንስ) ለመጠበቅ በዛ ያለ ያነሰ መጠን ሊኖራቸው ይችላል)፣
- በውጭ መቀመጫ ቦታና የመንገደኛ ግልጽ መተላለፊያ መካከል የ4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር) (ነጻ ቀጣናው በቀላሉ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ቀላል እቃዎች ሊቀመጥበት ይችላል)፣
- ከወንበሩ የኋሊት እስከ ከጎን ያሉ ጠረጴዛዎች የ6-ጫማ ቦታ
- በውጭ መቀመጫና በጎን ከሚገኝ ንግድ ፊተኛ ክፍል መካከል የ4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር) (አመልካቹ ከጎኑ ካለው ንግድ ፊት ለፊት እንዲያሰፋ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር)፣
- ነባር የእግረኛ መንገድ ካፌው የታዘጋ ካፌ ከሆነ የአየር ንብረት ምን ይሁን ምን ሁሌም እንደ ክፍት ካፌ በመሆን መስራት ይኖርበታል፣ እና
- ከእሳት መከላከያዎች 3-ጫማ ርቀት።

### መከልከያዎች

እንደነ ፓርክሌት ለመሳሰሉ በመኪና ማቆሚያ መስመር ለተስፋፉ መቀመጫ በተመለከተ ዝርዝሮች ለማግኘት እባክዎ የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ፓርክሌት መመሪያዎች ይመልከቱ፣ እና በደረጃ-1 ከፍ ያለ መድረክ እንደማያስፈልግ ልብ ይበሉ፣ ነገር ግን ጊዝያዊ አመሪካንስ ዊዝ ዲስኤቢሊቲስ አክት (አ.ዲ.ኤ.) መወጣጫ ያስፈልጋል።

የብሎኩን ፊት በሙሉ ወይም ከዛ በላይ መቀመጫን የሚያሰፋ ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች የብሎኩ እያንዳንዱ ጫፍ በNCHRP 350-TL-1 ረዣዥም መከልከያዎች (ይህም ማለት በጀርሲ ወይም በውሀ የተሞሉ መከልከያዎች ማለት ነው) ያስፈልጋቸዋል። የዲስትሪክቱ ዲፓርትመንት ኦፍ ትራንስፖርቴሽን (ዲ.ዲ.ኦ.ቲ.) በጎዳና ምደባ፣ መጠን እና ፍጥነት ላይ በመመርኮዝ የመከልከያ ፍላጎቶችና መስፈርቶች ይወስናል። ሙሉውን ጎዳና በመዝጋት ሁሉንም የጉዞ መስመሮች ለስትሬቸሪ የሚባል መሸጫ ለመጠቀም ለማዘጋጀት ለሚፈለገው የ20-ጫማ የእሳት አደጋ መስመር መንገድ እንዲኖር ለማድረግ የከባድ ጭነት መኪና ከነ ሾፌር ያስፈልጋል።

አመልካቾች እንደነ ፕላንተርስ፣ በእንስራ ያሉ እጽዋቶች፣ የወተት ክሬቶች፣ የገለባ ባሮች፣ ወይም ተመሳሳይ ንድፍ ያላቸው ለማሳያ ብቻ የሚያገለግሉ ተጨማሪ በመሀከል የሚገቡ ነገሮች ማቅረብ ይችላሉ፣ እነዚህ ነገሮች ግን እንደ መከልከያዎች ተደርገው አይቆጠሩም።

### እቃዎች (ፈርኒቸር)

እቃዎች ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ እና የጠረጴዛ ጃንጥላዎች ሊያካትት ይችላል። 10-ጫማ x 10-ጫማ በላይ መጠን ያላቸው ዱንካኖች አይፈቀዱም።

### ክፍተት (ስፔሲንግ)

ጎን ለጎን ባሉ ጠረጴዛዎች መካከል ያለው ክፍተት 6-ጫማ መሆን ይኖርበታል፣ 6-ጫማ መጠን ያለው የመንገደኛ መተላለፊያም ሊኖር ይገባል።

## ስዕላዊ መግለጫዎች (ግራፊክ ደፒክሽንስ)

በሚከተሉት ገጾች ያሉ ስዕሎች የህዝብ ቦታ እንዴት ለተስፋፋ የምግብ ቤት መቀመጫ ጥቅም መዋል እንደሚችል ለማሳየት ተመሳሳይ የአካላት ስብስቦች ይጠቀማሉ።




ሰዎች በሚሰለፉበት ቦታ በሰልፍ መስመር ሰዎች በምን ርቀት መቆም እንዳለባቸው የሚያሳይ በየ 6-ጫማ ርቀት በወለሉ ምልክቶች ሊኖሩ ይገባል።

**መከልከያ**

የመንገድ ክፍል የሚጠቀሙ ምግብ ቤቶች ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ፈቃድ የሰጠው መከልከያ ይጠቀሙ።

**መከልከያ**


ጥቁር መከልከያዎች፣ ውሀ የተሞላ መከልከያ እንደሚያስፈልግ ያሳያሉ

**የኤ.ዲ.ኤ. መወጣጫ (ራምፕ)**


ማንኛውም በእግረኛ መንገድ ደረጃ ያልሆነ የውጭ መቀመጫ፣ ወደ መቀመጫው የሚያደርስ የኤ.ዲ.ኤ. መወጣጫ ሊኖር ይገባል።

## የምግብ ቤት መቀመጫ ክፍተት


ጎን ለጎን ባሉ ጠረጴዛዎች ያሉ ወንበሮች ርቀት ቢያንስ 6 ጫማ እስከሆነ ድረስ ምግብ ቤቶች ያላቸውን እቃዎች ለውጭ መቀመጫ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።





ጠረጴዛዎሹ መካከል ያለው ርቀት 6′ እያለ በወንበሮቹ መካከል ያለው ርቀት ከ 6′ በታች ከሆነ፡ በወንበሮቹ መካከል ያለው ርቀት 6′ ይሆን ዘንድ ያንቀሳቀሱዋቸው





በአንድ ጠረጴዛ ያሉ ወንበሮች መካከል ያለው ርቀት 6' ባይሆንም ምንም አይደለም




በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት 6' ሆኖ እያለ በጠረጴዛዎች መካከል ያለው ርቀት ከ6' ያነሰ ቢሆን፡ በጠረጴዛዎቹ መካከል ያለው ርቀት 6' ይሆን ዘንድ ያንቀሳቅሱዋቸው



# ነባር የእግረኛ መንገድ መቀመጫ ያላቸው ምግብ ቤቶች

**አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች**

ከጎን ያለው የመንገደኛ መተላለፊያ፡ 6 ጫማ


በጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡  6 ጫማ

በጠረጴዛዎች እና በመንገደኛ መተላለፊያ መካከል ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 4 ጫማ

**አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ**

በጠረጴዛዎች መካከል ግልጽ የሆነ የእግረኛ መንገድ ስፋት ነጻ ቀጣና (ባፈር)

በጠረጴዛዎች እና የመንገደኛ መተላለፊያ መካከል ያለው ነጻ ቀጣና (ባፈር)




የእግረኛ መንገድ መቀመጫ


# የእግረኛ መንገድ መቀመጫና የማንሻ (ፒክ-አፕ) ቀጣና (ዞን) ያላቸው ምግብ ቤቶች

## አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች

ከጎን ያለው የመንገደኛ መተላለፊያ፡ 6 ጫማ
በጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 6 ጫማ
በመስመር ላይ ባሉ ደምበኞች መካከል ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 6 ጫማ
በመንገደኛ መተላለፊያና ጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 4 ጫማ

## አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ

በጠረጴዛዎች መካከል ግልጽ የሆነ የእግረኛ መንገድ ስፋት ነጻ ቀጣና (ባፈር)
በጠረጴዛዎች እና የመንገደኛ መተላለፊያ መካከል ያለው ነጻ ቀጣና (ባፈር)
የደምበኞች ወረፋና ክፍተት




የእግረኛ መንገድ መቀመጫ ከምግብ-ማንሳት (ፒክ-አፕ)

# የፓርክሌት መቀመጫ ያላቸው ምግብ ቤቶች

**አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች**

ግልጽ ከጎን ያለ የእግረኛ መንገድ ስፋት፡ 6 ጫማ


የውጭ መቀመጫ ቦታ፡ 6 ጫማ ወይም ከዛ በላይ

በጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ርቀት፡ 6 ጫማ

**አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ**

ግልጽ የእግረኛ መንገድ ስፋት

የውጭ መቀመጫ መጠን




? ምልክት

እንግዳ ተቀባይ/ ትራፊክ ተቆጣጣሪ

የፓርክሌት መቀመጫ

# የፓርክሌት መቀመጫ ያላቸው ምግብ ቤቶች

**አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች**

ግልጽ ከጎን ያለ የእግረኛ መንገድ ስፋት፡ 6 ጫማ

የውጭ መቀመጫ ቦታ፡ 6 ጫማ


በጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ርቀት፡ 6 ጫማ

በእግረኞች መተላለፊያና ጠረጴዛዎች ሊኖር የሚገባ ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 4 ጫማ

**አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ**

ግልጽ የእግረኛ መንገድ ስፋት

መጠን ያለው የውጭ መቀመጫ




**?** ምልክት

እንግዳ ተቀባይ/ ትራፊክ ተቆጣጣሪ

የፓርክሌት መቀመጫ ያለው የእግረኛ መንገድ መቀመጫ

# የጠባብ መተላለፊያ መንገድ (አሊ) ኤክስቴንሽን


ይህ አማራጭ፣ መቀመጫን ለስርጭት ወደ ማይፈለጉ ተጨማሪ እግሮች ያሉዋቸው ጠባብ መተላለፊያ መንገዶች (አሊስ) ያስፋፋል። ይህ፣ ከውሱን ምግብ ቤቶች ወይም ከበርካታ ምግብ ቤቶች፣ ምግብ የሚሸጡ መኪናዎች (ፉድ ትራክስ)፣ ወይም በእግረኛ መንገድ የሚሸጡ ጉሊቶች አጠቃላይ መቀመጫ ጋር የተያያዘ መሆን ይችላል። ዲ.ዲ.ኦ.ቲ. የስርጭት ፍላጎቶችን ይመዝናል፣ ተገቢውን ነገር ለመወሰንም ከእሳት አደጋ ድንገተኛ አገልግሎቶች (ኤፍ.ኢ.ኤም.ኤስ.) ጋር ይተባበራል።

### አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች

- በጠረጴዛዎ መካከል ሊኖር የሚገባ ርቀት: 6 ጫማ
- የእሳት አደጋ መስመር: 20 ጫማ
- ለአገልግሎት መግቢያዎች ሊኖር የሚገባ ግልጽ መተላለፊያ: 6 ጫማ

### አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ

- የእሳት አደጋ መስመር
- የመቀመጫ ቦታ
- የተሸከርካሪ መከልከያዎች



# ፕላዛዎች


ይህ አማራጭ መቀመጫዎችን ወደ ሰፊ የህዝብ ቦታዎች ያስፋፋል። ይህ መቀመጫ ከተወሰነ ምግብ ቤት ወይም ከበርካታ ምግብ ቤቶች፣ ምግብ የሚሸጡ መኪናዎች (ፉድ ትራክስ)፣ ወይም በእግረኛ መንገድ የሚሸጡ ጉሊቶች አጠቃላይ መቀመጫ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ማመልከቻው በማህበረሰብ ድርጅት (ኮሙኒቲ ኦርጋኒዜሽን) መደረግ ይኖርበታል።

## አነስተኛ የማህበራዊ ርቀት ደረጃዎች

በጠረጴዛዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ርቀት፡ 6 ጫማ
ግልጽ የመንገደኛ መተላለፊያ፣ 6 ጫማ
ለግንባታ መግቢያዎች ግልጽ መተላለፊያ፡ 6 ጫማ
በመንገደኛ መተላለፊያና በጠረጴዛዎች መካከል ነጻ ቀጣና (ባፈር)፡ 4 ጫማ

## አስፈላጊ መለያያዎችን በቴፕ ምልክት ማድረግ የሚገባ

ግልጽ የእግረኛ መንገድ ስፋት
መቀመጫ ቦታ
ለግንባታ መግቢያዎች ግልጽ መተላለፊያ



# ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች


ስትሬቸሪ የሚባለው መሸጫ ከእያንዳንዱ ፓርክሌቶች ባሻገር ያሰፋል፣ እንዲሁም ደግሞ የሙሉውን ብሎክ አንድ ወይም ከዛ በላይ መስመሮች ይዘጋል። ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች ፌስቲቫሎች ወይም አንዴ-ብቻ የሚደረጉ የተለዩ ክስተቶች አይደሉም፣ ነገር ግን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጊዜ የዲስትሪክቱ ማህበራዊ ርቀት መስፈርቶች ያሟላ ደህንነቱ የተጠበቀ በቂ የነፋስ እንቅስቃሴ ያለበት የመመገቢያ አማራጭ የሚሰጥ ጊዝያዊ የመስመር ወይም መንገድ መዝጋቶች ማለት ነው። ስትሬቸሪ የሚባል መሸጫ በሚያስከትለው የትራንስፖርት ጫና ምክኒያት አብዛኛዎቹ መንገዶች ለስትሬቸሪ የሚባል መሸጫ ብቁ ላይሆኑ ይችላሉ፣ እና በዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ጠለቅ ላለ የትራንስፖርቴሽን ምዘና እና ውሳኔ ይዳረጋሉ።

### *ብቁ አመልካቾች*

ቢዝነስ መሻሻል ዲስትሪክት (ቢ.አይ.ዲ.)፣ ዋና ጎዳና (መይን ስትሪት) ድርጅት፣ ወይም የአከባቢ አማካሪ ኮሚሽኖች (ኤ.ኤን.ሲ.) ለመሆን ብቃት ያለው መሆን ይኖርበታል። ምግብ ቤቶች በተናጠል ለማመልከት ብቃት የላቸውም።

## የመስመር መዘጋት፡ አንድ ወይም ከዛ በላይ የጉዞ መስመሮች

የመኪና ማቆሚያ፣ ወይም የመኪና ማቆሚያ እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ የጉዞ መስመር ከተሽከርካሪ ትራፊክ ይዘጋል፣ ነገር ግን ሙሉውን መንገድ አይዘጋም።




ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች
አማራጭ 1
አንድ ወይም ከዛ በላይ የጉዞ መስመሮች መዘጋት

ምልክት

እንግዳ ተቀባይ/ ትራፊክ ተቆጣጣሪ

### *ስፍራዎች (ሎኬሽንስ)*

- ከፊተኛው የወለል-ደረጃ ጎዳና በግምት 75 በመቶ የሚሆነው ለንግድ ስራ ጥቅም ይውላል፣ እና
- የተሽከርካሪ ፍጥነት 25 ወይም ከዛ በታች ማይል በሰአት።

### *በሚከተሉት የመስመር መዘጋቶች አይፈቀዱም፡*

- ስቴት-አቋራጭ፣ ሌሎች ነጻ (ፍሪ) ወይም የፍጥነት (ኤክስፕረስ) መንገዶች፣ እና
- ሁለት የጉዞ መስመሮች ብቻ ያላቸው ባለ ሁለት አቅጣጫ (ቱ-ወይ) ጎዳናዎች ከተዘጉ ወደ አንድ አቅጣጫ (ዋን-ወይ) የተሽከርካሪ ዝውውር።

### *የጊዜ ቆይታ*

የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ እስካለ ድረስ 24 ሰአታት፣ ሰባት (7) በሳምንት።

### *ሁኔታዎች*

የመስመር መዘጋቶች፡

- በእሳት አደጋ መከላከያ መንገዶች፣ በእሳት መከላከያ ተደራሽነት፣ ወይም ሌላ የአስቸኳይ ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪ ዘንድ መጥፎ ተጽዕኖ የለውም፣ እና
- በግል ንብረት ተደራሽነት ላይ ጣልቃ አይገባም (ለምሳሌ፣ ድራይቭወይ መንገዶች፣ ማድረስ (ደሊቨሪ)/መጫኛ ቀጣናዎች (ዞኖች)፣ ማቆሚያ ጋራጆች)።

# የመስመር መዝጋት፡ ሁሉም የጉዞ መስመሮች

ሁሉንም የመንገዱ የመንጃ መስመሮች ለተሽከርካሪ ትራፊክ ለጊዜው ለተወሰነ ጊዜ ይዘጋል። ምግብ ቤቶች የመመገቢያ አገልግሎታቸውን ወደ ማቆሚያ መስመሮችና ወደ ሁሉም የጉዞ መስመሮች ያሰፋሉ።

## ***ስፍራዎች (ሎኬሽንስ)***

የወለል ደረጃ የጎዳናው ፊተኛ ክፍል 75 መቶኛ ወይም ከዛ በላይ ለንግድ ስራ የሚውል ብሎክ ከሆነ አመልካቾች የትርፍ-ጊዜ የብሎክ መዘጋት እንዲደረግ ማመልከት ይችላሉ።

የብሎክ መዘጋቶች በሚከተሉት አይፈቀዱም፡

- ስቴት-አቋራጮች (ኢንተርስቴትስ)፣ ሌሎች ነጻ ወይም ፈጣን መንገዶች (ፍሪወይስ ኦር ኤክስፐረስወይስ)፣ ወይም ዋና አርተርያል ግማጆች (ሴግመንትስ)፣
- የአደጋ ጊዜ መገልገያዎች ያላቸው የመንገድ ግማጆች (ለምሳሌ፣ የእሳት አደጋ ጣቢያ፣ የፖሊስ ጣቢያ፣ ወዘተ) እና
- የዳብሊው.ኤም.ኤ.ቲ.ኤ. የአውቶቡስ መንገዶች (የሜትሮባስ ዋና መንገዶች፣ የአከባቢ (ሎካል) መንገዶች፣ ወይም የመጓጓዣ መንገዶች (ኮሙረር ራውትስ))፣ የዲ.ሲ. ሰርኩሌተር መንገዶች፣ የዲ.ሲ. ስትሪትካር መንገዶች።

## ***የጊዜ ቆይታ***


የትርፍ-ሰአት የብሎክ መዘጋት መንገዱን ለተሽከርካሪ ትራፊክ በሚከተሉት ሰአታት ይዘጋል፡

- ሀሙስ እና አርብ ከ 4:00 ፒ.ኤም. እስከ 11:00 ፒ.ኤም. (ሀፒ አወር እና እራት)
- 10:00 ኤ.ኤም. ቅዳሜ እስከ 10:00 ፒ.ኤም. እሁድ (ቁርስ፣ ብራንች፣ ምሳ፣ እራት)

የሙሉ-ሰአት የብሎች መዘጋቶች ሁሉንም የጉዞ መስመሮች፣ ሙሉውን መንገድ ለተሽከርካሪ ትራፊክ ለ24 ሰአታት፣ ለሰባት (7) ቀናት በሳምንት ይዘጋሉ። ምግብ ቤቶች የመመገቢያ አገልግሎታቸውን ከተመደቡት የእሳት አደጋ መስመሮች በስተቀር በመላ መንገዱ ያሰፋሉ።

## ***ሁኔታዎች***

- መዘጋቶቹ በእሳት አደጋ መከላከያ መንገዶች፣ በእሳት መከላከያ ተደራሽነት፣ ወይም በሌላ የአስቸኳይ ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪ መጥፎ ተጽዕኖ አይኖራቸውም፣
- በማንኛውም በተመደበ የ20-ጫማ የእሳት አደጋ መስመር ከባድ የጭነት መኪና ከነ ሾፌር ይኖራሉ።
- መዘጋቶቹ በግል ንብረት ተደራሽነት ላይ ጣልቃ ሊገቡ አይገባም (ለምሳሌ፣ ድራይቭወይ መንገዶች፣ ማድረስ (ደሊቨሪ)/መጫኛ ቀጣናዎች (ዞኖች)፣ ማቆሚያ ጋራጆች)፣
- ምግብ ቤቶች የብሎኩ መዘጋት ከማለቁ በፊት እቃዎቻቸው ማምጣት ይኖርባቸዋል፣
- የዳብሊው.ኤም.ኤ.ቲ.ኤ. የአውቶቡስ መንገዶች፣ የዲ.ሲ. ሰርኩሌተር መንገዶች፣ እና የዲ.ሲ. ስትሪትካር መንገዶች ወደ ሌላ መንገድ ሊመሩበት የሚችሉ (ሪራውቲንግ) ጫና ግምት ውስጥ ማስገባት፣ እና
- በነዚህ የተወሰኑ ጊዜያት ለዲፓርትመንት ኦፍ ፓብሊክ ወርክስ (ዲ.ፒ.ኤስ.) የጎዳና ጽዳት ወይም በተወሰነ የጽዳት ቡድን ለሚደረግ መደበኛ ጽዳት ሁሉም በመንገዱ ያሉ ነገሮች መነሳት ይኖርባቸዋል።




? ምልክት

እንግዳ ተቀባይ/ ትራፊክ ተቆጣጣሪ

ስትሬቸሪስ የሚባሉ መሸጫዎች
አማራጮች 2 እና 3
የሁሉም መስመሮች መዘጋት፡ የትርፍ-ሰአት እና ሙሉ-ሰአት

## ምዝገባና ፈቃድ

ሁሉም አዲስ ወይም የተስፋፋ የውጭ በታ የሚጠይቁ ምግብ ቤቶች በcoronavirus.dc.gov/phaseone መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ከምዝገባ በኋላ ነባር የእግረኛ መንገድ ካፌ ፈቃድ ያላቸው ንግድ ቤቶች ይህንን የምዝገባ ማረጋገጫ እንዳገኙ ስራዎቻቸው ለመጀመር ይፈቀድላቸዋል። ሌሎች ንግድ ቤቶች ከምዝገባ በኋላ የህዝብ በታ ፈቃድ ይሰጠኝ ብለው በ tops.ddot.dc.gov በኦንላይን ማመልከት ይኖርባቸዋል።

| የህዝብ በታ አጠቃቀም | ምዝገባ የሚያስፈልገው የጎግል ቅጽ | በቶፕስ የሚያስፈልግ ፈቃድ | በቶፕስ ያሉ የፈቃድ አይነቶች | ስራዎች መቼ መጀመር ይችላሉ |
|---|---|---|---|---|
| ነባር የእግረኛ መንገድ ካፌ - ለፔሪሜትር ለውጥ የለም | አይ | አይ | አይመለከትም | ወድያው |
| የተስፋፋው በታ የሚጠቀም ነባር የእግረኛ መንገድ ካፌ | አዎ | አዎ | ጊዝያዊ የእግረኛ መንገድ ጠረጴዛ አገልግሎት* | ምዝገባውን ሲያጠናቅቁ |
| አዲስ የእግረኛ መንገድ ጠረጴዛ አገልግሎት | አዎ | አዎ | ጊዝያዊ የእግረኛ መንገድ ጠረጴዛ አገልግሎት* | ምዝገባውን ሲያጠናቅቁ |
| ፓርክለት | አዎ | አዎ | ፓርክለት** | ፈቃድ ሲሰጥ |
| ስትሬቸሪ የሚባል መሸጫ | አዎ | አዎ | ሌላ ልዩ ዝግጅት* | ፈቃድ ሲሰጥ |
| ፕላዛዎችና ጠባብ መተላለፊያ መንገዶች (አሊስ) | አዎ | አዎ | ሌላ ልዩ ዝግጅት* | ፈቃድ ሲሰጥ |

*በቶፕስ የመስራት ፈቃድ (ኦኩፓንሲ) ክፍል የሚገኝ
**በቶፕስ የህዝብ በታ ኪራይ/አመታዊ ፈቃድ ክፍል የሚገኝ

## የኢንሹራንስ መስፈርቶች

ሁሉም የውጭ መቀመጫ በታዎች ያላቸው የንግድ ቤቶች የኢንሹራንስ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እባክዎ ተገቢውን ምድብ ይለዩ፣ ከታች ባለው ሰንጠረዥ እንደ ቀረበው ተገቢውን ሽፋኖች እንዳለ የሚያረጋግጥ የኢንሹራንስ ሰርተፊኬትም ያስረክቡ።

በተጨማሪ የኢንሹራንስ ሰርተፊኬቱ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት እንደሚከተለው እንደሆነ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡

- የሰርተፊኬቱ ባለቤት እንደሆነ ተደርጎ እንደ ተሰየመ።
- ተጨማሪ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዳለው ተደርጎ እንደ ተሰየመ።
- ምትክ ከመስጠት (ሳብሮጌሽን) ነጻ የሚል ተሰጥቷል።

ጥያቄዎች – orm.insurance@dc.gov

***ምግብ ቤት/የእግረኛ መንገድ ከፌ፣ ከሱቅ ፊት በተጨማሪ (አልኮል አይስተናገድም)፡***

| የሽፋን | ክስተት ገደብ | አጠቃላይ ገደብ |
|---|---|---|
| አጠቃላይ ሀላፊነት (ጀነራል ሊያቢሊቲ) | $1,000,000 | $2,000,000 |
| የመኪና ሀላፊነት (አውቶ ሊያቢሊቲ) (የሚመለከት ከሆነ) | $1,000,000 | አይመለከትም |
| ጃንጥላ ሀላፊነት (አምብሬላ ሊያቢሊቲ) | $2,000,000 | $2,000,000 |

***ምግብ ቤት/የእግረኛ መንገድ ካፌ፣ ከሱቅ ፊት በተጨማሪ አልኮል ይስተናገዳል፡***

| የሽፋን | ክስተት ገደብ | አጠቃላይ ገደብ |
|---|---|---|
| አጠቃላይ ሀላፊነት (ጀነራል ሊያቢሊቲ) | $1,000,000 | $2,000,000 |
| የመኪና ሀላፊነት (አውቶ ሊያቢሊቲ) (የሚመለከት ከሆነ) | $1,000,000 | አይመለከትም |
| የአልኮል መጠጥ ሀላፊነት (ሊከር ሊያቢሊቲ) | $1,000,000 | $1,000,000 |
| ጃንጥላ ሀላፊነት (አምብሬላ ሊያቢሊቲ) | $3,000,000 | $3,000,000 |

## ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

***ነባር ወይም የተስፋፋ የውጭ መቀመጫ ያለው ምግብ ቤት መቼ ስራ መጀመር ይችላል?***
*ከአርብ፣ መይ 29፣ 2020 ጀምሮ እያንዳንዱ በእግረኛ መንገድ በታ ነባር ወይም የተስፋፋ ውጭ መቀመጫ ያለው ምግብ ቤት በኦንላይን በ coronavirus.dc.gov መመዝገብ ይኖርበታል፣ የምዝገባው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላም ወዲያው ለመከፈት ብቁ ናቸው። መቀመጫቸውን እያሰፋ የሌሉ ምግብ ቤቶች መመዝገብ አያስፈልጋቸውም።*
*በታቀደው የጠርዝ ወይም ጉዞ መስመር መስራት ከመጀመራቸው በፊት ፓርክሌቶች እና ስትሬቸሪስ የተባሉ መሸጫዎች ተጨማሪ የቶፕስ ማመልከቻና ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።*

***ኤ.ኤ ን.ሲ. የሚመዝናቸው የትኞቹ የፈቃዶች አይነቶችን ነው?***
*የነዚህ የህዝብ ቦታዎች መጠቀሞች ጊዚያዊ ከመሆናቸው አንጻር ከ3ኛ ደረጃ ስትራቸሪስ የተባሉ መሸጫዎች በስተቀር የኤ.ኤ ን.ሲ. ምዘና ግዴታ አይደለም።*

***ፈቃዶቹ ለምን ያህል ጊዜ ያገለግላሉ?***
*ሁሉም የውጭ መቀመጫና ማንሻ/ማድረሻ (ፒክ-አፕ/ድሮፕ-ኦፍ) ከማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ጋር በጁላይ 24፣ 2020 አገልግሎታቸው ያበቃል፣ ነገር ግን ሊታደሱ ይችላሉ።*

***"የ6-ጫማ መመሪያው" በምግብ ቤት መቀመጫ እንዴት ይሰራል?***
*ደምበኞች በአንዲት ወንበር አብረው የተቀመጡ ከሆነ በ6-ጫማ ርቀት መቀመጥ አያስፈልጋቸውም። በቦታው ተገቢ ክፍፍል ካልተደረገ በስተቀር እያንዳንዷ ጠረጴዛ ከሌሎች ጠረጴዛዎች ቢያንስ በ6-ጫማ ርቀት መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣ ርቀቱ የሚለካው ከያንዳንዱ ወንበር የኋላ እግር፣ ከወንበር-እስከ-ወንበር፣ ነው።*

***በጎዳና የማንሻ (ፒክ-አፕ) ቦታ እና ፓርክሌት ሊኖረኝ ይችላል?***
*አዎ፣ በምግብ ቤቱ ለሁለቱ ጥቅሞች ለማግኘት በቂ የተሽከርካሪዎች ቦታዎች እንዲኖር የሚፈቅድ ነባር ልኬቶች እና የከጎን ያሉ ንግዶች ድጋፍ ላይ መሰረት በማድረግ።*

***ፓርክሌቶች ከእግረኛ መንገድ እኩል ደረጃ ይሆኑ ዘንድ ከፍ ያለ መድረክ ያስፈልጋቸዋል?***
*አይ፣ እነዚህ ጊዚያዊ ፓርክሌቶችና ስትራቸሪስ የተባሉ መሸጫዎች መድረክ እንዲኖራቸው አያስፈልግም፣ ነገር ግን ከእግረኛ መንገድ ወደ መቀመጫ በታ የሚወስድ ተንቀሳቃሽ የኤ.ዲ.ኤ. መወጣጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።*

***<u>ከአልኮላዊ መጠጥ ደንብ አስተዳደር (አብራ) ጋር የተያያዘ</u>***

***ማን ነው ለመሳተፍ ብቁ የሆነ?***
*የህንጻ ውስጥ የችርቻሮ ፈቃዶች (የስብሰባ ማዕከል (ኮንቬንሽን ሰንተር) የምግብና አልኮል ቸርቻሪዎች፣ ሆቴሎች፣ ብዙ-ነገሮች የሚደረጉባቸው ተቋማት (ማልቲ-ፐርፐዝ ፋሲሊቲስ)፣ የምሽት ክለቦች፣ የግል ክለቦች፣ ምግብ ቤቶች፣ እና ታቨርኖች)*

***ባለ ፈቃዶች ፈቃድ ያላቸውን የእግረኛ መንገድ ካፌዎቻቸው ወይም ሳመር ጋርደኖቻቸውን ማስፋት ይችላሉ?***
*አዎ- ነገር ግን ሁሉም ባለ ፈቃዶች መጀመሪያ መመዝገብና የፈቃድ ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርባቸዋል። መቀመጫን ወደ ህዝብ ቦታ ማስፋት የሚፈልጉ ባለ ፈቃዶች (እግረኛ መንገድ፣ ፓርክለት፣ ወይም የተመደበ የምግብና የችርቻሮ ቀጣና (ዞን)) የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ማረጋገጫ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። ወደ ግል ንብረት ማስፋት የሚፈልጉ ባለ ፈቃዶችም ተመሳሳይ የማመልከቻ ቅጽ መሙላት ይኖርባቸዋል፣ ነገር ግን የማይመለከቷቸውን ጥያቄዎች ያልፉ ዘንድ ይጠየቃሉ። በግል ንብረት ከውጭ ለመቀመጥ የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ማረጋገጫ ፈቃድ አያስፈልግም።*

**ጣሪያዎች (ሩፍታፕስ) ብቁ ናቸው?**
አዲስና የሰፋ የውጭ መመገቢያ መቀመጫ የሚፈቀደው በወለልና በጎዳና ደረጃ ባሉት ብቻ ነው። እንደ ሳመር ጋርደን ሆነው ለማገልገል ነባር ፈቃድ ያላቸው ጣሪያዎች (ሮፍታፕስ) ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ እና እንደነ የመቀመጫ ውቅሮች፣ የደምበኛ ወረፋ አያያዝ፣ እና የጥላ ቅርጾች ጨምሮ ሁሉም ከላይ ያሉ መመሪያዎች ይመለከቷቸዋል።

**ባለ ፈቃዶች የውጭ መመገቢያ ቦታ መጋራት ይችላሉ?**
አይ።

**የተዘጋጀ ምግብ መስፈርት ኣለ?**
አዎ። ባለ ፈቃዶች ቢያንስ ሶስት (3) የተዘጋጀ የምግብ አይነቶች ያለው በጥቅም ላይ ያለ የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) ሊኖራቸው ይገባል፣ በአንድ ጠረጴዛም አንድ ወይም ከዛ በላይ የተዘጋጀ የምግብ አይነት እንዲገዛ ማስገደድ ይኖርባቸዋል። የተዘጋጁ የምግብ አይነቶች እንደነ ቺፕስ፣ ፕሪትዘልስ፣ ብስኩት፣ ከረሜላ፣ ወይም ለውዝ አይነት አስቀድመው የታሸጉ መክሰሶች መሆን አይችሉም። ማንኛቸውም የሚሸጡ እና/ወይም የሚስተናገዱ የምግብ አይነቶች ፈቃድ ባለው አካል በስራ ቦታው፣ ወይም ከስራ ቦታ ውጪ ፈቃድ ባለው አካል፣ ወይም በዲ.ሲ. ሄልዝ (ጤና) ምግብ ለመሸጥ እና/ወይም ለማስተናገድ ማረጋገጫ አለው ተብሎ በሚታመን አካል የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል። .

**ብዮብ ይፈቀዳል?**
አይ። ደምበኞች የራሳቸው የአልኮል መጠጦች ከማምጣትና ከመጠጣት የተከለከሉ ናቸው።

**የፈቃዱ የሰፋ የውጭ መመገቢያ ቦታ በነባር የማስማሚያ ስምምነት በሰፈሩ አንቀጾች ተገዢ ይሆናል?**
አይ።


**የፈቃዱ ነባር የእግረኛ መንገድ ካፌ ወይም የሳመር ጋርደን በነባር የማስማሚያ ስምምነት በሰፈሩ አንቀጾች ተገዢ ይሆናል?**
አዎ። ነባር የውጭ መመገብ ፈቃድ በተመለከተ በማስማሚያ ስምምነት ያሉ አካላት ለእስከ 180 ቀናት ድረስ የተወሰኑ አንቀጾች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ለኤ.ቢ.ሲ. ቦርድ አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ።

**አብራ በተመለከተ ተጨማሪ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች እዚህ ይገኛሉ።**

# አባሪ

## አባሪ 1፡ የመቀመጫ ቦታ ሳይት ፕላን ምሳሌዎችና ማረጋገጫ ዝርዝሮች

የመቀመጫ ቦታዎች ሳይት ፕላኖች በእግረኛ መንገድ (ሳይድዎክ) ያሉ የመንገደኛ መተላለፍያዎች፣ መቀመጫ ቦታዎች፣ እና በመቀመጫ ቦታ ያሉ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች መካከል ተገቢ ርቀቶች እየተጠበቁ እንደሆነ የሚያሳዩ ልኬቶች የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል። ከታች ያለው ምሳሌ በሳይት ፕላኑ መካተት ያለባቸውን ኤለመንቶችና ልኬቶች ያሳያል።




መቀመጫ ቦታዎች በበርካታ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች የሚመረመሩ የደህንነት መስፈርቶች ሟሟላት ይኖርባቸዋል። ከታች ተዘርዝረዋል፡

***1. ትክክለኛ የሳይት ፕላን (እና በአንዳንድ ጉዳዮች ከፍታዎች (ኢሊቬሽንስ))***

ሳይት ፕላኑ ሁሉንም በመቀመጫ ቦታ አከባቢ በህዝብ ቦታ ያለውን እያንዳንዱ ኤለመንት ማካተት ይኖርበታል፣ ሚዛኑን (ስኬሉን) ጠብቆም መሳል ይኖርበታል (አመልካቾች ለውጭ መቀመጫ ቦታዎች ሳይት ፕላኖችን ለማዘጋጀት የሚረዱ የናሙና እቅዶችን እና አብነትን ይመልከቱ)፡

- የንብረት መስመር
- የጎዳና ዛፎች
- የጎዳና  መብራቶች
- ጠረጴዛዎችና ወንበሮች
- የመቀመጫ ቦታን ለይቶ ማስመር
- የሰፋ መቀመጫ ቦታ ለይቶ ማስመር (ተገቢ ከሆነ)
- በቂ ማህበራዊ ርቀት የሚያሳይ ልኬት
- በመቀመጫ ቦታና ከጎን ያለው ግልጽ የመንገደኛ መተላለፊያ መካከል 4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር)

ማስታወሻ፡ ማሳጠፊያዎች፣ ጃንጥላዎች፣ ፕላንተሮች፣ እና አጥሮች እንዲደረግ ምክረ ሀሳብ ላላቸው ለሁሉም የውጭ መቀመጫ ቦታዎች ከፍታዎች (ኢሊቬሽንስ) ያስፈልጋሉ።

## *2. የቦታ አቀማመጥና እቃዎች*

የጠረጴዛዎች፣ ወንበሮችና የሌሎች እቃዎች የሚያርፉባቸው ቦታዎች በቦታው እቅድ (ሳይት ፕላን) ሊታይ ይገባል፣ የሚከተሉትን መስፈርቶችም ሟሟላት ይኖርባቸዋል፡

- ***ከጠረጴዛዎችና ወንበሮች መካከል የ6-ጫማ ርቀት***
- ***በመቀመጫ ቦታና በእግረኛ መንገድ ጎን ባለ ግልጽ የመንገደኛ መተላለፊያ መካከል የ4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር)***
- ***በመቀመጫ ቦታ ሁለቱም ጫፎችና የመቀመጫ ቦታ ጠርዝ መካከል የ4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር)***
- ***ከእግረኛ መንገድ እስከ በጃንጥላ፣ ድንኳን ወይም ካኖፒ (የሚመለከት ከሆነ) ያለውን ዝቅተኛ ነጥብ የ8-ጫማ ርቀት***
- ***ከእሳት መከላከያ መገናኛዎች የ3-ጫማ ርቀት***
- ***የመቀመጫ ቦታዎች እስከ 36 ኢንች ርዝመት ባለው በጊዝያዊ የፕላንተር አጥር ሊታጠሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን***
- ***በሁሉም ጎኖች ከ36 ኢንቾች በላይ ክፍት መሆን ይኖርባቸዋል፡***
- ***ሁሉም ፕላንተሮች ከፍተኛ ቁመት (ይህ በፕላንተሩ ውስጥ ያለውን እጽዋት ያካትታል) 36 ኢንቾች***
- ***ባብዛኛው ንድፋቸው ክፍት መሆን ያለባቸው የሁሉም አጥሮች ከፍተኛ ቁመት 36 ኢንቾች***
- ***በመቀመጫ ቦታ ወይም በመቀመጫ ቦታ አቅራቢያ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ አይፈቀድም።***

## *3. ከእግረኛ መንገድ ጎን ስፋት*

በመቀመጫ ቦታ ዙሪያ ያለው ግልጽ የእግረኛ መንገድ በመቀመጫ ቦታውና ባቅራቢያ ያለው እንደነ የመንገድ መብራት፣ የተክል ሳጥን፣ ወይም የደንብ ምልክት ፖል የመሳሰሉ መሰናክል (ኦብስትራክሽን) ቢያንስ የ10-ጫማ ስፋት ሊኖረው ይገባል።

- በመቀመጫ ቦታና ከጎን ያለው ግልጽ የመንገደኛ መተላለፊያ መካከል ቢያን የ4-ጫማ ነጻ ቀጣና (ባፈር ዞን)
- በነጻ ቀጣናው (ባፈር ዞኑ) እና በቅርብ ከሚገኘው መሰናክል (ኦብስትራክሽን) መካከል የ6-ጫማ ግልጽ የመንገደኛ መተላለፊያ
- በአጠገብ ካለው የአውቶቡስ ማቆሚያዎች 15-ጫማ

# አባሪ 2፡ አግባብነት ያላቸው በስራ ላይ ያሉ ደንቦችና ደረጃዎች

ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፊት ዲስትሪክቱ የህዝብ ቦታን በተመለከተ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች አውጥቶ ነበር። እነዚህ ደንቦች ሰራተኞችን (ስታፍ) በዚህ ሰነድ መመሪያዎች እንዲያወጡ ረድቷል፣ እንዲሁም ደግሞ ወረርሽኙ ከጠፋ በኋላ የህዝብ ቦታ ደንብ እንዴት እንደሚሆን አመልካቾች እንዲረዱ በማድረግ ይረዳል። እባክዎን ከታች ተዘርዝረው ያሉትን በዚህ ጊዜ በስራ ያሉ የህዝብ ቦታ ደንቦች ይመልከቱ።

***አጠቃላይ***

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የማዘጋጃ ቤት መመሪያዎች፣ ታይትልስ 11፣ 12-A፣ እና 24

የህዝብ ሪም ንድፍ መመሪያ

የዲ.ዲ.ኦ.ቲ. ንድፍ እና ኢንጂነሪንግ መመሪያ

ስትሪትስኬፕ ንድፍ መመሪያዎች

***የእግረኛ መንገድ ካፌዎች***

***የፓርክሌት መመሪያዎች***

***የማቆሚያ ቀን ዝግጅት መመሪያዎች***

**የብሎክ ፓርቲ (በደረጃ-1 አይፈቀድም) ለማጣቀሻ ብቻ**